

# NEXT STEP ምንድነው?

**1. በትምህርት መጀመሪያ ላይ፤**

ለ Family Connection (ቤተሰብ ግንኙነት) ከልጅዎ አስተማሪ ጋር ይገናኙ። ይህ እርስ በእርስ ለመተዋወቅ ዓብይ ዕድል ነው።

+ ልጅዎ በፕሪስኩል ወይም መዋለ ሕጻናት ውስጥ ተሳትፎ ከነበረ፣ ከቅድመ-ትምህርት አስተማሪ ያገኙት መረጃ ካለ፣ እባክዎን ያካፍሉ።
+ እንዲሁም፣ ልጅዎን አስመልክቶ ሊኖርዎት የሚችል ማንኛውም የግምገማ መረጃ ካለዎት ደግሞ ለማካፈል ይሞክሩ።

**2. በኅዳር ወር መጀመርያ ላይ፤**

የልጅዎ አስተማሪ ስለልጅዎ ምን እንደ ተማረ ወይም እንደ ተማረች ለማወቅ፣ የ WaKIDS ሂደትን ተጠቅመው ይጠይቋቸው።

አስተማሪውን ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች ዓይነት ይጠይቋቸው፤

+ ልጄ በደምብ ማድረግ ስለሚችለው ነገር የተማሩት ምንድን ነው?
+ በትምህርት ክፍል ውስጥ የሚሰራውን ስራ ለማገዝ እቤት ውስጥ ምን ማድረግ እችላለሁኝ?

# የአገልግሎት ምንጮች፤

የ WaKIDS ዌብሳይት
www.k12.wa.us/WaKIDS

“Introducing Me!” የቤተሰብ ግንኙነት ቃለ ምልልስን መመሪያ መጽሔት
http://bit.ly/1maywqE

Washington State የቅድመ ትምህርት እና እድገት መመሪያዎች፥ ከልደት እስከ 3ኛ ክፍል
https://bit.ly/39RcMt0

አዲስ በሚጀምሩ የዜሮ ክፍል (ኪንደርጋርተን) ተማሪዎች ላይ ዘወትር የሚታዩ ጸባዮችና በ WaKIDS መስፈርቶች የሚለኩ
https://bit.ly/3bTsCFk

WaKIDS እና የዋሽንግተን ስቴት መመዘኛዎች
https://bit.ly/2SPNshw

---

Washington State Department of Children, Youth, and Families

WaKIDS | Washington Kindergarten Inventory of Developing Skills
360-725-6161

## ለልጅዎ ብሩሕ ተስፋ ይሄውልዎት።

የዜሮ ክፍል (ኪንደርጋርተን) ለልጅዎ ታላቅ ተሞክሮ እንዲሆን፣ ከእኛ ጋር አብረው በመስራትዎ በጣም እናመሰግንዎታለን!

2013
13-0032



# ዜሮ ክፍል (ኪንደርጋርተን) መግባት

ለእርስዎና ለልጅዎ ዓብይ ምዕራፍ ነው!

## በመሆኑም፣ ተጋብዘዋል

... ልጅዎ በትምህርት ቤት እንዲሸጋገርና እንዲበለጽግ ሊረዳ በሚችል በታቀደ የፕሮግራም ላይ እንዲሳተፉ።

---

ወደ **WaKIDS** የጀብደኝነት ታሪክ እንኳን ደህና መጡ

# WaKIDS
## ምንድን ነው?



**ምን፤** WaKIDS.

**መቼ፤** ልጅዎ ልክ ዜሮ ክፍል (ኪንደርጋርተን) እንደገባ።

**የት፤** በአዲሱ የልጅዎ ትምህርት ቤት።

**ለምን፤** ምክንያቱም አብረን በመሥራት፣ ለዕድሜ ልክ ትምህርት በጣም የሚቻለውን ጅመራ መፍጠር እንችላለን።

የዋሽንግተን የኪንደርጋርተን የሞያዎች ማዳበሪያ መንገድ (Washington Kindergarten Inventory of Developing Skills) — ወይም WaKIDS — የሚከተሉትን ለማከናወን የሚያገለግል ሂደት ነው፤

- ተማሪዎችንና ቤተሰቦቻቸውን ወደ ኪንደርጋርተን ለመቀበል።
- የተማሪዎችን ጠንካራ ጎን ለመገምገም።
- ልጆች በትምህርት ቤት  የተሳካላቸው እንዲሆኑ በሊያስችሏቸው የልጆች የዕድገትና ትምህርት ጸባዮች ላይ መወያየት።

እንደ እርስዎ አድርጎ ልጅዎን የሚያውቀው ማንም የለም። እርስዎ፣ የልጅዎን ትምህርት  የሚደግፈውንና ወደ ኪንደርጋርተን ሽግግርን በተቻለ መጠን ቀላል የሚያደርገው ቡድን ዋና አባል ነዎት።





# WaKIDS
Washington Kindergarten Inventory of Developing Skills

## የድል ጎዳና፤

### የቤተሰብ ግንኙነት

እርስዎንና ልጅዎን ለመተዋወቅ፣ ቤተሰቦችና አስተማሪዎች አብረው ይሰራሉ።

### የመላው ልጅ ግምገማ

ድጋፍ በጣም አስፈላጊ የሚሆንበት ላይ ለማተኮር አስተማሪዎች የልጆችን ጠንካራ ጎኖችን ለይተው ያውቃሉ።

### ለቅድመ ትምህርት ትብብር

ልጆች የተሳካላቸው እንዲሆኑ ለመርዳት የዜሮ ክፍል (ኪንደርጋርተን) አስተማሪዎችና የቅድመ-ትምህርት አገልግሎት አቅራቢዎች መረጃዎችን ይካፈላሉ።

### ውጤቱ

ለልጅዎ የትምህርት ስኬት ጎዳናን መቀየስ።